***The Ethio-Canadian Forum for Democracy Ottawa, Canada***
***የኢትዮ-ካናዳዊያን የዲሞክራሲ መድረክ በኦታዋ ካናዳ***
***ottawa.forum@gmail.com      Tel. 613 867 9292***

# <u>በኦታዋ-ካናዳ የኢትዮጵያኖች ቁጣ !</u>

ከሩቅ እያስገመገመ አካባቢውን የሚያናውጠው ድምፅ እየተቃረበ በመምጣቱ መሃል ኦታዋ መናጥ ጀምራለች ። ጡሩምባው ፣ ፊሽካው ፣ ፉጨቱ በህብረት ያስተጋባል ። ኢትዮጵያኖች በአንድነት ሆነው ቁጣቸውን እየገለጡ ናቸው ።
ኦክቶበር 11፣ 2011 ከረፋዱ 11፡30 ጀምሮ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ዘር ሳይለይ በህብረት ተቃውሞውን ለመግለፅ በካናዳ የውጪ ጉዳይ መስሪያ ቤት ፊትለፊት ተሰብስቦ ብሶቱን ያሰማል ።

- መለስ ዜናዊ ቴረሪስት ነው !
- ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ !
- የህዝብ ልሳን የሆኑ ጋዜጠኞች በአስቸኳይ ይፈቱ !
- ካናዳ ለሽብርተኛው የመለስ ዜናዊ መንግስት የምታደርገውን እርዳታ ታቁም !



የመሳሰሉት የብሶት ድምፆች በአካባቢው ላይ በከፍተኛ ድምፅ ይስተጋባሉ ። የሃገራቸው የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል ፣ ፍትህና እኩልነት በዚያች አገር መስፈን አለበት ፣ ለሰብዓዊ መብት መጠበቅና በአገራችን ዲሞክራሲ መስፈን አለበት ብለው ቆርጠው በተነሱ ኢትዮጵያውያኖች ላይ የሚታየው እልህና ቁርጠኝነት ኢትዮጵያችን ዛሬም የወላድ መካን እንዳልሆነች ያረጋግጣል ።

የአሜሪካ ድምጽ የአማርኛው ፕሮግራም ፣ የአዲስ ድምፅ ሬድዮ ፣ ከረንት አፌርስ ፣ ቃሌ የውይይት ክፍልና ከፍተኛ ተደማጭነት ያላቸው መገናኛ ብዙሃን አንቴናቸውን ተክለው ከዚያው ከካናዳ የውጪ ጉዳይ መስሪያ ቤት ፊት ለፊት በቀጥታ የተቃውሞ ሰልፉን እየዘገቡ ነው ።

የካናዳ ቴሌቪዥንና ሲቲኤን ጨምሮ የተለያዩ ሚዲያዎች በተቃውሞ ሰልፈኞቹ መካከል በመዘዋወር ቃለ መጠይቅ ያደርጋሉ ። ኢትዮጵያውያኖች ቆርጠዋል ። አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ባንዲራችንን አንገቱ ላይ እንደ ማተብ ያላሰረና ከፍ አድርጎ የማያውለበልብ አንድም የአገር ተወላጅ አይታይም ።

ኢትዮጵያውያኖች ልዩነታቸውን ወደ ጐን ማድረጋቸውንና የጋራ ጠላታቸውን በህብረት ለመፋለም መዘጋጀታቸውን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል ። የኢትዮ-ካናዳውያን ፎረም ለዲሞክራሲ ስብስብ ለዚህ ያለአንዳች ልዩነት የእጅ ለእጅ የመያያዝ ህብረት ዋናው መሰረት ነው ። ይህ ስብስብ ወደፊትም በአገራችን የፖለቲካ መድረክ ጉልህ ሚና ይጫወታል ተብሎ ከፍተኛ ተስፋ ይጣልበታል ።
ቀደም ብሎ ከውስጡ መርጦ ያዘጋጃቸው ሶስት አባላትን ያካተተ ቡድን የተቃውሞ ስብሰባውን ዓላማና በመለስ ዜናዊ መንግስት አማካኝነት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እየተካሄደ ያለውን የከፋ ሽብርተኝነት የካናዳ መንግስትና ህዝብ እንዲያውቀው ለማስረዳትና የተዘጋጀውንም ደብዳቤ ለካናዳ መንግስት ተወካይ በእጅ ለመስጠት በመጠባበቅ ላይ ናቸው ።



የኢትዮጵያውያን የብሶት ድምፅ አካባቢውን እያናወጠ ባለበት ሰዓት በካናዳ መንግስት የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ተወካይ በስሜት በመነካትና በከፍተኛ አክብሮት ሰላማዊ ሰልፈኞቹን በመወከል የቀረቡትን ሶስት አባላት ተቀብለው ካነጋገሩ በኋላ ለመንግስታቸው የተዘጋጀውን ደብዳቤ በመቀበል ፤ በተጨማሪም ካሁን በፊት ይደረግ እንደነበረው አሁንም ከኢትዮጵያውያኖች ጋር በቀጣይ በጠረጴዛ ዙሪያ በመቀመጥ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ስለ ኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት አያያዝና የዲሞክራሲን ግንባታ በተመለከተ ለመወያየት ቃል ገብተው በመጡበት አኳኋን ተመልሰዋል ።

በኦታዋ በኢትዮ-ካናዳውያን የተካሄደው የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ የሽብርተኛውን የመለስ ዜናዊን መንግስት የሰብዓዊ መብት ጥሰት በማጋለጥ ደረጃ ግቡን መምታቱንና ኢትዮጵያውያኖችን በዘር ሳይከፋፍል ልዩነታቸውን ወደ ጐን በመተው በአንድነት እጅ ለእጅ ያስተሳሰረ እንደነበረ ከቦታው ሆነን ለመዘገብ ችለናል ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !
በኦታዋ የኢትዮ-ካናዳውያን ፎረም ለዲሞክራሲ
ኦክቶበር 12፣2011